# 2ኛ ዮሐንስ (20)

## ጥናት አንድ (2ኛ ዮሐ 1-6)

የጥናት ዓላማ:- ክርስቶስ በውስጤ አለ የሚለው ሃሳብ ከቃል ያለፈና ሌሎቹን የእግዚአብሄር ቤተሰቦች በመውደድ መመላለስ ምርጫ የሌለው ትዕዛዝ እንደሆነ ለመመልከት::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «በእውነት ለምወዳት እኔ ብቻ ሳልሆን እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ለሚወዷት...በውስጣችን ከሚኖር...እውነት የተነሳ» 2ኛ ዩሐ 1-2

1. 2ኛ ዮሐ 1-6ትን በአንድነት አንብቡት:: በመጀመሪያዎቹ አራት ቁጥሮች ውስጥ ውነት የሚለው ቃል አራት ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን:: በዚህ ምንባብ መሰረት እውነት ማለት ምን እንደሆነ ነው የምትረዳው?
2. ይህች ሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክቱን የተጻፈላትና የተወደደችው ሴት ማነች ብለህ ታምናለህ? ለምን?
3. እኔ እወዳታለሁ ሌሎችም ሰዎች ሁሉ ይወዷታል» የሚለው አነጋገር በቁ1 ላይ ከምናነበው ሃሳብ ጋራ ልዩነት ታይበታለህ ወይ? ከሆነስ ይህ ልዩነት ምንድነው?
4. በዚሁ ቁ1 ላይ እውነትና ፍቅር የተጣመሩ ነገሮች እንደሆኑ ይጠቁመናል:: በምን መንገድ ነው እውነትና ፍቅር በአንድነት መሄድ ያለባቸው?
5. በዚህ ምንባብ ውስጥ ሐዋርያው ዮሐንስን በጣም ደስ ያሰኘው ነገር ምንድነው? በራስህ ህይወት ስታይ በአማኝ ላይ ምን ስታይ ነው እጅግ ደስታን የሚሰጥህ?
6. በቁ5 ላይ ጸሐፊው ለምንድነው ቀድሞ የምታውቀውን አሮጌ ነገር ደግሞ መጻፍ ያስፈለገው ለምን አዲስ ነገር አልጻፈም?
7. በቁ5-6 ያለው ሀሳብ በቁ1-2 ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ በማነጻጸር ግንኙነታቸውን አስረዳ::
8. ከዛሬው ጥናት በልብህ ውስጥ ክርስቶስ ንዳለ ለማረጋገጫነት ሊረዳ የሚችል ምን ሃሳብ አይተሃል? በፍቅር መመላለስህን እንደ ምርጫ ወይስ እንደ ግዴታ ታየዋለህ? የዛሬው ትምህርት አረማመድህን በምን መንገድ እንደሚቀይረው አከፍል::

## ጥናት ሁለት (2ኛ ዮሐ 7-13)

የጥናት ዓላማ:- የሃሰት ትምህርት ሁልዜ ግልጽ ሆኖ የሚታይ እንዳልሆነና ከማንጠብቀውም አቅጣጫ ሊመጣ ስለሚችል ዘወትር የምንሰማውን በቃሉ መመርመር እንደሚኖርብን ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ: ‹‹በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና ከትምህርቱ የሚወጣ ሁሉ አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት የሚኖር ግን አብም ወልድም አለው፡፡›› 2ኛ ዮሐ ቁ9

1. 2ኛ ዩሐ 7-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-6 ላይ ያለውና ይህ ዛሬ የተነበበው ክፍል ተቃራኒ ሃሳቦችን ያዘሉ ናቸው ለማለት የሚያስችለን ነገር ምን እንደሆነ ትናገር፡፡
2. «...ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ወጥተዋል፡፡» ሐዋርያው ዮሀንስ እነዚህ አሳቾች ከየት ነው ወደ ዓለም ወጡ የሚለው?
3. ስለነዚህ አሳቾች ቁጥር አንድ የሚጠቁመን ቢያንስ ሶስት ሃሳቦች እናያለን፡፡ እነዚህን ሶስት ነገሮች አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ይህንን ቁጥር በተለይ ከይሁዳ መልዕክት ቁ4 ጋራ የሚያመሳስለው የትኛው ሐሳብ ነው?
4. በ2ኛ ዮሐ 7-13 መሰረት ለክርስቶስ ተቃዋሚ ዋነኛ መለያው ሆኖ የቀረበው ሃሳብ ምንድነው? እነዚህ ሰዎች ትኩረት እንዲሰጣቸውና ችላ መባል የሌለባቸው ምክንያት ለምንድነው?
5. በቁ7 ላይ የምናነበው አነጋገር በገላ 1:8 ከሚገኘው ሃሳብ ጋር የሚያመሳስለው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
6. በቁ8፤ ቁ9፤እና በቁ10-11 ላይ አማኝ ሊወድቅ የሚችልባቸው ሶስት አደጋዎች ሰፍረዋል፡፡ እነዚህ ምን ምን እንደሆኑ አስረዳ፡፡
7. ዘሬ ከጠናነው ክፍል ውስጥ በአንተ አመለከከት ትክክለኛ ትምህርት ይዞ መራመድ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የሚጠቁመን አንድ ክፍል የትኛው ነው?
8. ቁ10 ላይ የተጠቀሱት ሃሳቦች እርስ በርሳችን እንግዳን እንድንቀባበል ከታዘዝነው ሃሳብ ጋራ አይቃረንም ወይ? አስረዳ፡፡
9. በቤተ ክርስትያን ውስጥም ሆነ ውጭ የምትማረውን ትምህርት ወደ ውስጥህ ከማስገባትህ በፊት በእግዚአብሄር ቃል ምን ያህል ትመረምራለህ? የስህተት ትምህርት ከማትጠብቅበት ሥፍራ ሊመጣ ስለሚችል በጥንቃቄ መስማት ያስፈልጋል፡፡